# ባለ ሥልጣኑና የታክሲው ሹፌር !

አንዱ የወያኔ ባለሠልጣን ድንገት መኪናው ተበላሽቶበት ታክሲ መጠቀም ይገደድና አስቂሞ ይሳፈራል። በ6ኪሎ የሰማእታት ሃውልት ሥር እየተጠመዘዙ ሳለ ሃውልቱ ላይ ያሉት የሰማእታት ምስሎቹ ጥቂቶቹ አዲስ ቅብ ተቀብተው ቀሪዎቹ ደግሞ አለመቀባታቸውን ያስተዋለው ባለስልጣን ፥ ? .........! "

"ለምንድነው ጀምረው የሚተውት?" ከጀመሩ መጨረስ አልያም አለመ ጀመር ይሻላል በማለት አንገቱን አጠማዞ ሃውልቱን እየተመለከተ የወ ቀሳ አስተያየቱን ይሰጣል። ባለታክሲም ጨዋታኛ ቢጤ ኖሮ ሃውልቱን መልከት አድርጎ እንዲህ ይላል

" የተቀቡት በተሃድሶ ያመኑት የጠቅላይ ምኒስትሩ ደጋፊዎች ያልተቀ ቡት ደግሞ መበስበስን የመረጡት ውህዳኖች ወይም ሙሰኛ ሆነው የ ተገኙት የነሥዬ ደጋፊዎች ሳይሆኑ አይቀሩም" በማለት እራሱም ፈገግ እያለ ተሳፋሪውንም ሊያስቅ ሲሞክር ያላሰበው ነገር ተከተለ።

**ባለስልጣኑ** " አፍህ ዝጋና ሥራህን ሥራ ተሃድሶ ገለመሌ ውሻ ! "

**ሹፌር** "ምን ያሳድብሃል ካላሳቀህ አለመሳቅ እንጂ የምን ስድብ ነው?

**ባለስልጣን** " አተ አፍህ ዝጋ! ውሻ !......"

**ሹፌር** " አንተም አፍህን ዝጋ ! አትሳደብ"

**ባለስልጣን** " እዋ! አንተ ውሻ !.........ዛሬ "

**ሹፌር** " ውሻ አትበለኝ"

**ባለስልጣን** " እልሃለሁ ውሻ ! ውሻ ነህ ውሻ! ምናባክ ታመጣለህ?" ብሎ ሽጉጡን ከጎኑ ላጥ አድርጎ ይደግንበትና

**ባለስልጣን** " ውሻ እልሃለሁ ውሻ ነህ ምናባክ ታመጣለህ?"

**ሹፌር** " ምን አመጣለሁ አልኩኝ ውሻና ሰው ለይ አልኩኝ እንጂ"

ባለስልጣኑም ሽጉጡን እንደደገነበት " ሰው አይደለህም እኔ ውሻ ብዬሃለሁ በቃ ምን ትሆናለህ?"

**ሹፌር** " የግልህን አመለካከት ማንጸባረቅ መብትህ ነው"

**ባለስልጣን** " አንተ ዝምበል እዋ!...... ውሻ ብዬሃለሁ ውሻ ነህ"

ብሎ በሽጉጡ አፈሙዝ ጉንጩን ወጋ ሲያደርገው ባለታክሲው በድንጋጤ መንዳት ስላስቸገረው መኪናውን ወደ መንገድ ዳር ወጣ አድርጎ አቆመ።

ባለስልጣኑም አላፊ አግዳሚው እንዳያይ ሰግቶ " አታቁም ንዳ ንዳ ብያለሁ አንተ ውሻ ንዳ" እያለ ሽጉጡን ወደታች ዝቅ አድርጎ የሚመለከታቸው ሰው እንዳለ ለማረጋገጥ ዙሪያውን ገልመጥ ገልመጥ እያለ ሲመለካከትለት ፋታ ያገኘው ሹፌር " የት ሃገር ነው ውሻ መኪና የሚነዳው " በማለት የመኪናውን በር ከፍቶ እግሬ አውጭኝ ብሎ በመፈርጠጥ ከአጣብቂኙ ተርፏል።